**אמהרית**

**የ19ኛው ክኔሴት**
**ማዕከላዊ የምርጫ ኮሚቴ**

# የእስራኤል የምርጫ ሥርዓቶች

## የማዕከላዊ ምርጫ ኮሚቴ የመረጃ ወረቀት

መሠረታዊው የክኔሴት ሕግ 4፡ በምርጫው የሚመረጠው ክኔሴት የሚከተለው እንዲሆን ወስኗል።

**አጠቃላይነት** – ማንኛውም ዕድሜው ከ18 ዓመት በላይ የሆነ የአገሪቱ ዜጋ በምርጫዎች ላይ የመሳተፍ መብት አለው።

**ብሔራዊነት** – የምርጫዎቹን ውጤቶች ለማስላት ያስችል ዘንድ መላው እስራኤል እንደ አንድ የምርጫ ክልል ተደርጎ ይታያል።

**ቀጥተኛነት** – ተመራጮች የሚወሰኑት በቀጥታ ድምጽ አሰጣጥ መሠረት ነው (በተዘዋዋሪ የምርጫ ስልት ሕዝቡ መራጭ አካል የሚመርጥ ሲሆን ያ መራጭ አካል ደግሞ ተሿሚዎችን ይመርጣል። የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ምርጫ ጥሩ ምሳሌ ነው)።

**እኩል የሆኑ ናቸው** – እያንዳንዱ መራጭ አንድ ድምጽ አለው። ሁሉም መራጮች ምርጫው ላይ ተጽእኖ ለማሳደር እኩል ኃይል አላቸው።

**ምስጢራዊ** – ድምጽ አሰጣጡ ምስጢራዊ ነው። ድምጽ እንዴት አድርጎ እንደተሰጠ ከመራጩ ውጪ የሚያውቅ ሰው የለም። የድምጽ አሰጣጡን ምስጢራዊ የሚያደርጉት ነገሮች

- የድምጽ መስጫው ቦታ የተከለለ ሲሆን መራጩ የምርጫውን ወረቀት ፖስታው ውስጥ በሚከትበት ጊዜ ሌላ ሰው እንዳያየው ይሸፍነዋል።
- የታሸገ የድምጽ መስጫ ፖስታ። ይህ ፖስታ በውስጡ ምን ዓይነት ወረቀት እንደተቀመጠበት ለማየት አያስችልም።

> ***መራጩ በፈለገው ዓይነት ድምጽ መስጠት የሚችል ሲሆን እንዴት አድርጎ እንደመረጠ ሌላው ሰው ሊያውቅ አይችልም።***

**ልብ በሉ፡ ምርጫዎች የሚካሄዱት ሸቫት 11 ቀን 5773 ዓ.ዓ. ወይም ጃኑዋሪ 22 ቀን 2013 ዓ.ም. ነው።**

## የመምረጥ መብት

ማንኛውም የእስራኤል ዜጋ የሆነ እስራኤላዊ ኗሪና በክኔሴት ምርጫ ቀን ዕድሜው 18 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነ፣ በመራጮች መዝገብ የተመዘገበ ድምጽ የመስጠት መብት አለው።

በ19ኛው የክኔሴት ምርጫ ላይ በመራጮች መዝገብ ላይ ለመመዝገብ መብት የሚኖራቸው የሚከተሉትን 3 ነገሮችን የሚያሟሉ ናቸው።

(ሀ) የእስራኤል ዜጋ የሆነ፣ የእስራኤልን ዜግነት የተቀበለና ከኪስሌቭ 14 ቀን 5773 ዓ.ዓ. (18.11.2012) በፊት በሕዝብ መዝገብ ተመዝግቦ የሚገኝ
(ለ) ከጃኑዋሪ 22 ቀን 1995 በፊት የተወለደ
(ሐ) በእስራኤል አገር ኗሪነት ተመዝግቦ የነበረና ስሙና አድራሻው በእስራኤል ውስጥ ከኪስሌቭ 14 ቀን 5773 ዓ.ዓ. (18.11.2012) በፊት በሕዝብ መዝገብ ተመዝግቦ የሚገኝ ከሆነ

የመራጮች መዝገብ የምርጫ ቦታን ለማወቅ እንዲያስችል በኢንቴርኔት ድረ ገጽ ላይ ይቀርባል። መዝገቡ www.gov.il በተባለው ድረ ገጽ ላይ ይቀርባል።
መዝገቡ ግልጽ የሚሆንበት ጊዜ በተገቢው ወቅት የማዕከላዊ ምርጫ ኮሚቴ ድረ ገጽ በሆነው በwww.bechirot.gov.il ላይ ይቀርባል።

## ድምጽ የሚሰጠው የት ነው?

- እያንዳንዱ መራጭ የራሱን ስም በያዘ የምርጫ ጣቢያ ውስጥ ድምጽ መስጠት ይችላል። በምርጫው ቀንና ምርጫው ከመደረጉ በፊት የድምጽ መስጫው ትክክለኛ ቦታ የት እንደሆነ በማዕከላዊው የምርጫ ኮሚቴ ቴሌፎናዊ የመረጃ (ኢንፎርሜሽን) ቢሮ አማካይነት ማጣራት ይቻላል። የስልክ ቁጥሮቹም በጋዜጣ ላይ የሚታተም ሲሆን የማዕከላዊ ምርጫ ኮሚቴ ድረ ገጽ በሆነው በwww.bechirot.gov.il ላይም ይቀርባል።

- የአካላዊ እንቅስቃሴ ችግር ያለባቸው ሰዎች የአካላዊ እንቅስቃሴ ችግር ላለባቸው ሰዎች ተብለው በተዘጋጁ ድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ድምጽ መስጠት ይችላሉ። መራጩ ከድምጽ መስጫ ጣቢያ ፀሐፊ ፊት ቀርቦ አካላዊ እንቅስቃሴ ማድረግ እንደማይችል ካስታወቀ (ይህን የማያደርገው አካለ ስንኩልነቱ በዓይን ተለይቶ ሊታይ የማይችል ከሆነ ነው) በምርጫ ጣቢያው ውስጥ እንዲመርጥ ፈቃድ ይሰጠዋል።
  ከላይ በተጠቀሱት የመረጃ ቢሮዎችና የማዕከላዊ ምርጫ ኮሚቴ ድረ ገጽ አማካይነት የአካላዊ እንቅስቃሴ ችግር ላለባቸው ሰዎች የትኞቹ ድምጽ መስጫ ጣቢያዎች አመቺ እንደሆኑ ማጣራት ይቻላል። በእነዚህ ጣቢያዎች ምርጫው የሚደረገው ድርብ በሆኑ ፖስታዎች ነው።

- እንደዚሁም በምርጫ ጣቢያዎቹ ወታደሮች ድምጽ የሚሰጡ ሲሆን በሆስፒታሎች፣ በእስር ቤቶች፣ በጊዜያዊ ማገቻ ቦታዎችና ውጪ አገር በሚገኙ የእስራኤል ወኪል መሥሪያ ቤቶች ውስጥ ድምጽ ይሰጣል።

- ከምርጫው 3 ሳምንት አስቀድሞ ለእያንዳንዱ መራጭ የት ድምጽ እንደሚሰጥ ትክክለኛው የቦታው አድራሻ ይላክለታል። የድምጽ መስጫውን ቦታ ካርታ በድረ ገጽ ላይ ማየት ይቻላል።

## የምርጫው ቀን

የምርጫው ቀን ሥራ የማይሠራበት ቀን ነው። ቢሆንም ግን የሕዝብ ማመላለሻዎች በተለምዶው ዓይነት ይሠራሉ። በምርጫው ቀን የድምጽ መስጫ ቦታዎች ከጧቱ 7 ሰዓት እስከ ምሽቱ 10 ክፍት ናቸው። (በትናንሽ መንደሮችና የመራጮቹ ቁጥር ከ350 የማይበልጥ ከሆነ ድምጽ የሚሰጠው ከጧቱ 8 እስከ ምሽቱ 8 ሰዓት ድረስ ነው። በሆስፒታሎች፣ በእስር ቤቶች፣ በጊዜያዊ ማገቻ ቦታዎች ድምጽ የሚሰጠው እንደዚሁ ነው።) የድምጽ መስጫዎቹ ቦታዎች በሮች ልክ ከምሽቱ በ10 ሰዓት ላይ ይዘጋሉ (በትንንሽ መንደሮች በ8 ሰዓት)። ድምጽ ለመስጠት ሰልፍ ላይ ያሉ ሰዎች ድምጽ እንዲሰጡ ይፈቀድላቸዋል። ነገር ግን በሮቹ ሳይዘጉ ወደ ድምጽ መስጫው ቦታ የመጣና ተራውን ተሰልፎ የሚጠብቅ ሰው ድምጽ መስጠት ይችላል።

**እዚህ ላይ አጥብቀን የምናስገነዝበው ከድምጽ መስጫው መዝጊያ ሰዓት በኋላ የሚመጣ ሰው ድምጽ መስጠት አይችልም።**

ድምጽ የሚሰጠው ሰው ተለይቶ ሊታወቅ የሚችለው ከሚከተሉት መንገዶች ውስጥ በአንዱ <u>ብቻ</u> ነው፡፡

- የድምጽ ሰጪው ፎቶ ያለበት መታወቂያ ወረቀት.
- የድምጽ ሰጪው ፎቶ ያለበት የእስራኤል ፓስፖርት.
- የድምጽ ሰጪው ፎቶ ያለበትና ጊዜው ያላለፈበት የእስራኤል መንጃ ፈቃድ.

## <u>የድምጽ መስጫ ሳጥንና የተከለለ የድምጽ መስጫ ቦታ</u>

የድምጽ አሰጣጥ ሂደቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

(ሀ) መራጩ ለአስመራጩ ኮሚቴ ፀሐፊ ራሱን በመታወቂያ ወረቀት አማካይነት ያስተዋውቃል።

(ለ) መራጩ ስሙ በመራጮች መዝገብ ውስጥ የሚገኝ ከሆነ "የ19ኛው ክኔሴት ምርጫ" ተብሎ የተጻፈበትና ሰማያዊ ቀለም ያለው የምርጫ ፖስታ ይቀበላል። የድምጽ መስጫ ስታዎች የተዘጉና ከውስጥ የጠቆሩ ሲሆን የማዕከላዊ ምርጫ ኮሚቴና የማዕከላዊ ምርጫ ኮሚቴ ሊቀ መንበር ማኅተም አለባቸው፡፡ እንደዚሁም የአስመራጩ ኮሚቴ 2 አባላት የእጅ ፊርማም አለባቸው፡፡

(ሐ) መራጩ ወደ ድምጽ መስጫው የተከለለ ቦታ ውስጥ ይገባል። ወደ ድምጽ መስጫው የተከለለ ቦታ የሚገባውም ለብቻው ነው፡፡ ማንም ሰው ከእሱ ጋር እንዲገባ አይፈቀድለትም። በበሽታና ሌላ አካላዊ ችግር የተነሣ በምርጫው ቦታ ውስጥ እንቅስቃሴ ሊያደርግ የማይችል ሰው በድምጽ አሰጣጥ ሂደት የሚረዳውን ሰው ለማምጣት ይፈቀድለታል። ነገር ግን የሚረዳው ግለሰብ የአዛውንት ተጧሪዎች መኖሪያ ወይም ማንኛውም እርዳታ የሚያሻው ድምጽ ሰጪ በሚኖርበት ተቋም ውስጥ የሚሠራ ሠራተኛ ወይም ሥራ አስኪያጅ መሆን የለበትም። ይህን እርዳታ የሚሰጠው ሰው በምርጫው ቀን ከ2 በላይ ሰዎችን ለማጀብ አይችልም።

(መ) መራጩ ከፊት ለፊቱ ለክኔሴት ዕጩ የሆኑ ፓርቲዎች ድምጽ መስጫ ወረቀቶች ተቀምጠው ያገኛል። እንደዚሁም በድምጽ መስጫው ውስጥ ነጭና ባዶ ድምጽ መስጫ ወረቀቶችም ይገኛሉ።

## <u>የክኔሴት ድምጽ መስጫ ወረቀት – ለሁሉም ፓርቲዎች</u>

ድምጽ የሚሰጠው ለፓርቲዎች ብቻ ነው፡፡ በያንዳንዱ ድምጽ መስጫ ወረቀት ላይ የፓርቲው ስምና የሚወክለው ፊደል ወይም ፊደላት ተጽፈዋል። የፓርቲዎች ስም (መጠሪያ) እና ፊደላቶቻቸው በጋዜጣ ላይ የሚታተሙ ሲሆን በማዕከላዊ ምርጫ ኮሚቴ ድረ ገጽ ላይም ይቀርባሉ።

**ድምጽ የሚሰጠው በሚከተለው መንገድ ነው**

(ሀ) ድምጽ ሰጪው እሱ ሊመርጠው የሚፈልገው ፓርቲ ስምና ፊደል ያለበት **አንድ የድምጽ መስጫ ወረቀት ብቻ** ይመርጣል። ከዚያም ያንን ወረቀት በክኔሴት ምርጫ ፖስታ ውስጥ ይከተዋል። መራጩ ፖስታውን መዝጋት አለበት። መራጩ ከፈለገ በነጭና ባዶ የድምጽ መስጫ ወረቀትም መጠቀም ይቻላል። በዚያም ወረቀት ላይ የሚመርጠውን ፓርቲ ፊደልና ስም ይጽፋል (መጻፍ የሚችለው በዕብራይስጥ ወይም በዓረብኛ ብቻ ነው)።

(ለ) መራጩ ከተከለለው ቦታ ውስጥ በመውጣትና በእጁ የታሸገውን ፖስታ በመያዝ ወደ ድምጽ መስጫ ሳጥን በመቅረብ የኮሚቴው አባላት እያዩት ፖስታውን ወደ ድምጽ መስጫ ሳጥን **በገዛ እጁ** ይከትታል።

(ሐ) መራጩ የሥነ ሥርዓት አስከባሪዎቹን ትእዛዝ መስማት አለበት።

ለምርጫው ፖስታ አንድ የድምጽ መስጫ ወረቀት ብቻ መክተት ያስፈልጋል። በአንድ ፖስታ ውስጥ ሁለት የአንድ ፓርቲ ድምጽ መስጫ ወረቀቶች ቢገኙ ድምጹ አይሰረዝም (ነገር ግን አንድ ወረቀት ብቻ ነው ከግምት የሚገባው)። ነገር ግን በፖስታው ውስጥ ከ2 በላይ የአንድ ፓርቲ ድምጽ ወረቀቶች ወይም የተለያዩ ፓርቲዎች ድምጽ መስጫ ወረቀቶች ቢገኙ **ድምጹ ይሰረዛል።**

**የምርጫ ውጤቶች**

1. ከተጣሩት ድምጾች ከፍፍል ቢያንስ 2% የተቀበሉ ማንኛቸውም ፓርቲዎች በማንዳት (מנדט) ክፍፍል ላይ ይሳተፋሉ።
2. በክፍፍሉ ላይ የሚሳተፉት ፓርቲዎች የተጣሩ ድምጾች ለ120 የሚካፈል ሲሆን በማካፈል የሚገኘው ውጤት ቁጥር "መለኪያ" (מודד) ይሆናል።
3. ሁሉም ፓርቲ የሚያመጣው ድምጽ በመለኪያው ውጤት ከተከፋፈለ በኋላ ተገቢውን የማንዳት (מנדט) ቁጥር ያሸንፋል
4. ቀጥሎም ትርፍ ድምጾች በሕጉ መሠረት ይከፋፈላሉ።

> ማስታወስ የሚያስፈልገው፡ ለክኔሴት የሚደረግ ምርጫ በእስራኤል የዲሞራሲያዊ ሂደት ከፍተኛው ምዕራፍ ነው። በዚህም ቀን እያንዳንዱ/እያንዳንዷ ዜጋ ድምጽ የመስጠት መብታቸውን ተግባራዊ እንዲያደርጉ የሚጋበዙ ሲሆን በዚህም ዓይነት ለመጪዎቹ ዓመታት የእስራኤልን ዲሞክራሲ ቅርጽ ያሲዛሉ። ስለዚህ ለውጥ ለማምጣት መጥታችሁ ድምጻችሁን ስጡ!

የመጀመሪያው (ኦሪጂናል) የዕብራይስጥ ጽሑፍ

**የ 19ኛው ክኔሴት**

**ማዕከላዊ የምርጫ ኮሚቴ**

www.bechirot.gov.il

"የ 19ኛው ክኔሴት ምርጫ" መረጃ ወረቀት የአማርኛ ትርጉም

ለአዲስ ገቢዎች አገልግሎት ተብሎ የተዘጋጀ

**የአዲስ ገቢዎች ማስተናገጃ መሥሪያ ቤት፣ የኅትመት ክፍል**

www.klita.gov.il

**ኢየሩሳሌም 2013 – መብቱ የተጠበቀ ነው – ©**